የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፴ ቀን ፪ሺ.፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.6
ADDIS ABABA 9th Junuary, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፩፻፷፫/፪ሺ.፲፪ ዓ.ም

የመድን ሥራ /ማሻሻያ/ አዋጅ............ገጽ ፲፪ሺ.፸፩
ማረሚያ ቁጥር ፲፬/፪ሺ.፲፪......................ገጽ ፲፪ሺ.፸፯

**Content**

Proclamation No. 1163/2019

Insurance Business (Amendment) Proclamation ... Page 12071
Corrigendum No.14/2020........................... Page 12077

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፩፻፷፫/፪ሺ.፲፪

## የመድን ሥራ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፮/፪ሺ.፬ን ማሻሻል አስገፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የመድን ሥራ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፩፻፷፫/ ፪ሺ.፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ማሻሻያ**

የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፮/፪ሺ.፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና (፲፪) ተሰርዘው በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች ተተክተዋል:-

፰/ "ኩባንያ" ማለት በንግድ ሕግ የተሰጠውን ትርጉም የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆኑ የውጭ ዜጎች ወይም በኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆኑ የውጭ ዜጎች በጋራ የተያዘ ወይም ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆኑ የውጭ ዜጎች የተያዘ ወይም በኢትየጵያውያን እና የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆኑ የውጭ ዜጎች በጋራ ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ፣

## PROCLAMATION No. 1163/2019

## A PROCLAMATION TO AMEND INSURANCE BUSINESS PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Insurance Business Proclamation No.746/2012;

**NOW, THEEFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may by cited as "Insurance Business (Amendment) Proclamation No. 1163/2019."

2. **Amendment**

The Insurance Business Proclamation No.746/2012 is hereby amended as follows.

1/ Sub Article (8) and (12) of Article 2 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub Articles (8) and (12):

8/ "company" means a share company as defined under the Commercial Code, the capital of which is owned fully by Ethiopian nationals or foreign nationals of Ethiopian origin or jointly owned by Ethiopian nationals and foreign nationals of Ethiopian origin, or organizations owned fully by Ethiopian nationals or foreign nationals of Ethiopian origin or

በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ አክሲዮን ማኅበር ነው፣

፲፪/ "የፋይናንስ ድርጅት" ማለት መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት፣ በዲጅታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ወይም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት በዚህ ዘርፍ ሥር የሚመደብ ሌላ ድርጅት ነው፣

፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፴፯) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፴፰፣ ፴፱፣ ፵፣ ፵፩፣ ፵፪፣ ፵፫፣ ፵፬፣ ፵፭፣ እና ፵፮) ተጨምረው ከንዑስ አንቀጽ ፴፰ እስከ ፵ ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከ፵፯ እስከ ፵፱ ሆነው ተሸጋሽገዋል:-

፴፰/ "በዲጅታል ዘዴዎች የሚሰጥ የፋይናንስ አገልግሎት" ማለት በዲጅታል ዘዴዎች የሚሰጡ የክፍያ፣ የሐዋላ እና የመድን አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፣

፴፱/ "ታካፉል" ማለት ሰዎች የተወሰነ የገንዘብ መዋጮ ከማህበራቸው አባሎች በመሰብሰብ በአባሎቻቸው ላይ ለሚደርስ ጥፋት (loss) ወይም ጉዳት(damage) ቀደም ብሎ በተወሰነ የገንዘብ ልክ ለመርዳት የሚያቋቁሙት ኅብረት ነው፣

፵/ "የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ" ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፻፺፬ ላይ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፣

፵፩/ "መድን ሰጪ ኩባንያ" ማለት የመድን ሥራ እንዲሰራ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ መድን ሰጪ ነው፣

፵፪/ "አነስተኛ መድን" ማለት መሰረታዊ የመድን መርሆዎችን የሚከተል፣ በአረቦን ክፍያ ላይ የተመሰረተ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች

jointly owned by Ethiopian nationals and foreign nationals of Ethiopian origin,

12/ ''financial institution" means an insurance company, a bank, a micro finance institution, a capital goods finance company, a reinsurer, a micro insurance provider, postal savings, money transfer institution, digital financial service provider or such other institution as determined by the National Bank;"

2/ The following new Sub-Articles (38, 39, 40, 41, 42, 43, 44, 45, and 46) are added after Sub Article (37) of Article 2 of the Proclamation, and the subsequent Sub-Articles (38) to (40) are renumbered as Sub Articles (47) to (49), respectively:

38/ "digital financial service" means financial services including payments, remittances and insurance accessed and delivered through digital channels;"

39/ "**takaful**" means a cooperation between members of a community whereby each member undertakes to contribute a certain sum of money to a fund which will be used mutually to assist the members against a defined loss or damage;

40/ "foreign national of Ethiopian origin" means a foreign national of Ethiopian origin as defined under Proclamation No. 270/2002 Providing Foreign Nationals of Ethiopian Origin with Certain Rights to be Exercised in their Country of Origin;"

41/ "insurance company" means a company licensed by the National Bank to undertake insurance business or an insurance company owned by the Government;"

42/ "micro insurance" means any form of protection against risks that is designed for and accessed by low-income people, provided by different categories of

፵፫/ "አነስተኛ መድን ወኪል" ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው እና አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አነስተኛ መድን ሰጪዎች ስም የሚሰራ እና አነስተኛ መድን ገቢዎችን እና አነስተኛ መድን ሰጪዎችን የማገናኘት ስራ የሚሰራ ሰው ነው፡

፵፬/ "አነስተኛ መድን ሰጪዎች" ማለት የአነስተኛ መድን ሥራን ለመስራት ብቻ የተቋቋሙትን ጨምሮ መድን ሰጪ ኩባንያዎች እና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ናቸው፡

፵፭/ "የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ (ፕሪሚየም)" ማለት በመድን ፖሊሲ ውስጥ የተገለጸውን ሽፋን ለመስጠት መድን ሰጪ የሚያስከፍለው ገንዘብ ነው፡

፵፮/ "ዕዳን መክፈል የሚያስችል ወሰን" ማለት በእያንዳንዱ አብይ የመድን ሥራ ዓይነት ተቀባይነት ያለው ሀብት ተቀባይነት ካለው ዕዳ ሊበልጥበት የሚገባው ወሰን ነው፡

፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፱) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲) ተጨምሯል፡፡

፲/ ብሔራዊ ባንክ ለአነስተኛ መድን ሰጪና ለአነስተኛ መድን ወኪል ስለሚሰጥበትና ቁጥጥር ስለሚካሄድበት ሁኔታ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፲ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲ ተተክቷል፡፡

፲/ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በመድን ሥራ ስለሚሳተፍበት ሁኔታ፦

በአንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፭) ላይ የተጣለው ክልከላ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣

፩/ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም ሙሉ በሙሉ የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለቤትነት ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያን የጋራ ባለቤትነት የተቋቋመ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ መድን ሰጪ ኩባንያ የአክሲዮን ባለቤት ወይም መድን ሰጪ ኩባንያ ማቋቋም ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው አግባብ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ

43/ "micro insurance agent" means a person licensed by the National Bank as a micro insurance agent who, acts for and on behalf of one or more micro insurance providers, and engages in intermediary services;"

44/ "micro insurance providers" means insurers, including those dedicated to deal in micro insurance business and microfinance institutions;"

45/ "premium" means the amount of money an insurer charges to provide the coverage described in an insurance policy;"

46/ ''margin of solvency" means the excess of admitted assets over admitted liabilities to be maintained for each main class of insurance business;"

3/ The following new Sub Article (10) is added after Sub Article (9) of Article 5 of the Proclamation;

10/ "The National Bank may issue a directive prescribing the manner of licensing and supervising micro insurance provider and micro insurance agent."

4 / Article 10 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new article 10:

10/ Manner of participation of a Foreign National of Ethiopian Origin in an Insurance Business

Without Prejudice to the prohibition laid down under Sub Article (5) of Atricle 16 of the proclamation,

1) "A foreign national of Ethiopian origin or an organization owned fully by foreign nationals of Ethiopian origin or jointly by foreign nationals of Ethiopian origin and Ethiopian nationals are allowed to acquire the shares of Ethiopian insurer or to open an insurance company;

2) If a foreign national of Ethiopian origin holds a share directly in an insurance company or indirectly by holding a share

ኢትዮጵያዊ በቀጥታ በመድን ሰጪ ኩባንያ የአክስዮን ባለቤት ሲሆን ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የአክስዮን ባለቤት የሆነበት ሌላ ድርጅት የመድን ሰጪ ኩባንያ ባለአክስዮን ሲሆን የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በድርጅቱ የሚኖረው የአክስዮን ድርሻ ዋጋ በሙሉ ተቀባይነት ባለው የውጭ ምንዛሪ ብቻ የሚከፈል ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ግዴታ ቢኖርም፡-

ሀ) ከአክስዮን ባለቤትነት የሚገኝ የትርፍ ድርሻ፣

ለ) የአክስዮን ድርሻውን ለሌላ ሰው ሲያዛውር፣

ሐ) ባለአክስዮን የሆነበት መድን ሰጪ ኩባንያ ሲሸጥ ወይም ፈርሶ ሲጣራ፣ ወይም

መ) ሌሎች ከአክስዮን ባለቤትነት ጋር በተያያዘ፣

የውጭ ሀገር ዜግነት ላለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሚከፈሉ ማናቸውም ዓይነት ክፍያዎች በሙሉ በብር የሚከፈለው ይሆናል፣ እንዲሁም በዚህ አግባብ የሚያገኘውን ሀብት ወይም ጥቅም ወደ ውጭ ማዛወር አይፈቀድለትም፡፡

፬/ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በመድን ሰጪ ኩባንያ ውስጥ መዋዕለ ንዋያቸውን በሥራ ላይ ስለሚያውሉበት ተጨማሪ ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሰርዟል፡፡

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ሐ) ተሰርዞ በሚከተለው ፊደል ተራ (ሐ) ተተክቷል፡፡

ሐ) "የመድን ሰጪ ዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነትና ግዴታዎችን እና የመድን ሰጪ ኩባንያን መልካም የኩባንያ ሥራ አመራርን፣"

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተተካ ሲሆን ከንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭)

in another organization that holds a share in an insurance company, in accordance with the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a foreign national of Ethiopian origin or the organization to which he is a shareholder, shall pay the values of the shares in an insurance company only in an acceptable foreign currency;

3) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, all types of payments due to a foreign national of Ethiopian origin resulting from;

a) dividends earned from a share in an insurance company;

b) transfer of shares in an insurance company;

c) sales or liquidation of an insurance company; or

d) any other matters related to shareholding in an insurance company;

shall be paid to him in a local currency, i.e. Birr; meanwhile, he may not be allowed to repatriate any asset or interest obtained in this manner.

4) The National Bank may issue directive related to additional conditions for investment in an insurance company by foreign nationals of Ethiopian origin."

5/ Sub Article (5) of Article 12 of the Proclamation is repealed.

6/ Paragraph (c) of Sub Article (4) of Article 15 of the Proclamation is deleted and replaced by new paragraph (c);

c) "the duties and responsibilities of board of directors and manner of corporate governance of an insurance company;"

7/ Sub Article (3) of Article 16 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub Article (3) and new Sub Article (5) is added after sub Article (4);

፫) "ማናቸውም መድን ሰጪ ዳይሬክተር በተመሳሳይ ጊዜ የሌላ ፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም። በተጨማሪም ዳይሬክተሩ አሥር በመቶና ከዚያ በላይ የባለቤትነት ድርሻ የያዘበት የንግድ ድርጅት የመድን ሰጪ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

፭) "የውጭ ሀገር ዜጎች ወይም በከፊልም ሆነ በሙሉ በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶች ወይም የውጭ መድን ሰጪ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የመድን ሥራ ማካሄድ ወይም የመድን ሥራ የሚያካሂዱ ቅርንጫፎች ማቋቋም እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ መድን ሰጪዎች የአክስዮን ባለቤት መሆን አይችሉም።"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዟል።

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዟል።

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል።

፩/ "በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር መድን ሰጪው ለማንኛውም ዳይሬክተር፣ ባለአክስዮን፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ኦዲተር፣ አስሊ ወይም ለማንኛውም የመድን ረዳት ወይም ከነዚህ ሰዎች ጋር ግንኙነት ላለው ማንኛውም ሰው ለመድን ሰጪው ኩባንያ ሰራተኞች ሁሉ ከተፈቀደ የሰራተኞች ጥቅማጥቅም በስተቀር ማናቸውንም ዓይነት ብድር ወይም የገንዘብ ዋስትና ሊሰጥ አይችልም። ሆኖም ይህ ገደብ መድን ሰጪው የገባውን የሕይወት መድን ውል ዋጋ መጠን ሳያልፍ ለሕይወት መድን ገቢዎች የሚሰጠውን ብድር አይጨምርም።"

፲፩/ ከአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ቀጥሎ አዲስ አንቀጽ ፶፭፣ ፶፮፣ ፶፯፣ ፶፰፣ ፶፱፣ ፷ ተጨምረው ከአንቀጽ ፶፭ እስከ ፷ ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፷፩ እስከ ፷፮ ሆነው ተሸጋሽገዋል።

፶፭. <u>የጠለፋ መድን ሰጪን ስለመቆጣጠር</u>

፩/ ብሔራዊ ባንክ የጠለፋ መድን ሰጪን ይቆጣጠራል።

3) "A director of an insurer may not, at the same time, serve as a director of another financial institution. Moreover, a business entity or a company in which such director has ten percent and more equity interest may not serve as a director of an insurer."

5) "Foreign nationals or organizations fully or partially owned by foreign nationals may not be allowed to open an insurance company or carry on insurance business or operate branch offices or subsidiaries of foreign insurers in Ethiopia or acquire the shares of Ethiopian insurers."

8/ Sub Article (1) of Article 26 of the Proclamation is repealed.

9/ Sub Article of (1) Article 30 of the Proclamation is repealed.

10 Sub Article (1) of Article 46 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1):

1/ "Unless otherwise provided by regulations or directives issued pursuant to this Proclamation, no insurer may grant any loan or financial guarantee, except employment benefits allowed to all employees of an insurer or loans on life policies issued by him within their surrender value, to any director, shareholder, chief executive officer, auditor, actuary or to any insurance auxiliary or to any other person connected with such persons."

11/ The following new Articles (55, 56, 57, 58, 59, 60) are added after Article 54 of the Proclamation and the subsequent Articles 55 to 60 are renumbered as Articles 61 to 66, respectively .

**55. <u>Supervision of A Reinsurer</u>**

1/ The National Bank shall supervise a reinsurer.

፪/ ብሔራዊ ባንክ የጠለፋ መድን ሰጪን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆነ መመሪያ ያወጣል፡፡

፫/ ከአንቀጽ ፮(፪-፭)፣ ፳፯(፫)፣ ፴፬ (፪)፣ ፴፱-፵፭፣ ፵፰-፶፣ ፶፰ እና ፶፱ (እንደተሻሻለው) በስተቀር ሁሉም የአዋጁ ድንጋጌዎች በጠለፋ መድን ሰጪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፶፮. <u>በዲጅታል ዘዴዎች የመድን አገልግሎት ስለመስጠት</u>

በዲጅታል ዘዴዎች የመድን አገልግሎት ስለሚሰጥበት ሁኔታ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ይወስናል፡፡

፶፯/ <u>የማስታወቂያ ይዘትን ስለመቆጣጠር</u>

ማናቸውም መድን ሰጪ በማናቸውም ጊዜ በብሔራዊ ባንክ እምነት ሐሰተኛ፣ አሳሳች፣ አደናጋሪ ወይም የሌላውን ጥቅም የሚጎዳ የተከፈለበትን የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ማስታወቂያ፣ ፖስተር፣ ቢልቦርድ፣ በራሪ ወረቀት፣ ሰርኩላር ወይም ሌላ ሰነድ እና የተከፈለበትን የጋዜጣ እና የመጽሄት ማስታወቂያ አውጥቶ ቢገኝ መድን ሰጪው ማስታወቂያውን እንዲያቋርጥ፣ እንዲያሻሽል ወይም ከማስተዋወቅ እንዲቆጠብ ብሔራዊ ባንክ ሊያዘው ይችላል፡፡

፶፰/ <u>የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ (ፕሪሚየም) ስለመወሰን</u>

ብሔራዊ ባንክ ዝቅተኛ የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ ለመወሰን ይችላል፡፡ ዝቅተኛ የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ ስለሚወሰንበት ሁኔታ በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፶፱/ <u>የመድን አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብት ጥበቃ</u>

የመድን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት እና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል መመሪያ ብሔራዊ ባንክ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፷/ <u>ለታካፉል መድን ሰጪ ኩባንያ ፈቃድ ስለመስጠት እና ስለመቆጣጠር</u>

፩/ በአዋጁ የመድን ሥራን ለመሥራት እና ለመቆጣጠር የተደነገጉ ድንጋጌዎች እና መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ብሔራዊ ባንክ የታካፉል መድን ሥራ ለሚሰራ መድን ሰጪ ፈቃድ ስለሚሰጥበት እና ቁጥጥር ስለሚያካሄድበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዴታዎችን ለመደንገግ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

2/ The National Bank shall issue directive necessary to supervise a reinsurer.

3/ All Articles of this Proclamation are applicable to a reinsurer licensed under the Proclamation except Articles 6 (2-5), 27 (3), 34 (2), 39-45, 48-50, 58 and 59 (as amended).

**56. <u>Digital Insurance Services</u>**

Minimum conditions to provide digital insurance services shall be determined by a National Bank directive.

**57. <u>Regulation of Advertisement</u>**

The National Bank may at any time direct an insurer to withdraw, amend or refrain from issuing a paid radio or television announcement, a poster , billboard, brochure, circular, or other document, and a paid advertisement in a regularly published newspaper or magazine that it considers to be false, misleading, deceptive, or offensive.

**58. <u>Determining Insurance Premium</u>**

The National Bank may determine an economic (minimum) premium rate in a manner to be specified by a directive.

**59. <u>Insurance Services Consumer Protection</u>**

The National Bank may issue directive for protecting the right and interest of insurance service consumers.

**60. <u>Licensing and Supervision of A Takaful Insurance Company</u>**

1/ Without prejudice to the requirements specified under the provisions of the Proclamation and directive the National Bank shall issue directive to prescribe additional conditions for the licensing and supervision of a takaful insurance company.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ብሔራዊ ባንክ ከመደበኛው የመድን ሥራ ጋር የታካፉል አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመቆጣጠር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**ማረሚያ ቁጥር ፲፬/፪ሺ፲፪**

የኢትዮጵያ ምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፷፭ (፩) (ሀ) "፬ መቶ ሺ መስራች አባላት ሲኖሩት፡" የተባለው "፬ ሺ መስራች አባላት ሲኖሩት፡" ተብሎ ይነበብ።

2/ without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the National Bank may issue directive to regulate takaful insurance carried on alongside a conventional insurance business.

3. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 9th day of Junuary 2020**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**Corrigendum No.14/2020**

Article 65 (1) (a) of the Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct Proclamation No. 1162/2019 Amharic version which read as "it has 400,000 founding members;" is hereby corrected and shall be read as "it has 4000 founding members;"